## *ስለራሱ እማይናገረው ታሪክ ሰሪ ህዝብ !*



*ስለራሱ እማይናገረው ታሪክ ሰሪ ህዝብ ሌሎች ሲያሞግሱትም ያመሰግናል እንጂ አይኮፈስም። ካሳ ጥንቅሹ ዝንተ አለም እዉነት ሆኖ እሚኖር ንግግር ያደረገው አምና ነበር። እምባ እየተናነቀኝ ነው ያዳመጥኩት፤ በቃል እማልገልፀው ስሜት ነበር የተሰማኝ። ይህን ንግግር በየቀኑ ብሰማው ዉሎ ሙሉ ያደርገዋል። እስኪ እናንተም አንብቡት።*

*ትምክህተኞች በትግራይ ህዝብ በጨለምተኝነት የሚዘምቱት እና በሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ በጥርጣሬ እንዲታይ ሌትተቀን የሚጣደፉ ፀሀያቸውን ስላጨለመባቸው ነው፡፡ አይፈረድባቸውም ታሪክ ምን ተፈጠረ ነው እንጂ የሚዳሰሰው ምን ቢሆን ይሻል ነበር በሚል አይፃፍም፡*

*በመሆኑም አምባገነኑ የደርግ ስርአት ለመገርሰስ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በየፌናው ታግለዋል ነገር ግን እንደ ትግራይ ህዝብ እና ህወሓት ግን አልታገልንም፡፡*

*ከኢህአፓ ተገንጥለን ከህወሓት ጋር ለመመካከር በሄድንበት ወቅት ጥርጣሬ ነበረን ከምክክር በውሃላ ያገኘነው ግን ተደራጅተን እንድንታገል አስፈላጊውን ድጋፍ ያደረገልን ህወሓት ነበር፡፡*

*የትግራይ ህዝብ ለራሱ ነፃነት ብቻ ሳይሆን ለመላ ኢትዮጵያውያን ነው የታገለው፡፡ለራሱ ብቻ ቢሆንማ እኮ ትግራይ ከደርግ አገዛዝ በ1981 ዓ.ም ሙሉበሙሉ ነፃ ወጥታ ነበረች፡፡የትግራይ ምርጥ ልጆች እነ አሞራው እና ቐሺ ገብሩ በደብረታቦር እና መራኛ ውድ ሂወታቸው የከፈሉት ለኢትዮጵውያን ነበር፡፡*

*የትግራይ ህዝብ የሦስት ሺ ታሪክ እንደሚነግረን በኢትዮጵያዊነቱ የሚኮራ እና የኢትዮጵያዊነት እሴት ከማንም በላይ ጠቡቆ የኖረ ህዝብ ነው፡፡"*

*ታጋይ ታደሰ ካሳ( ጥንቅሹ)*